22110014

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Monday 16 May 2011 (morning)
Lundi 16 mai 2011 (matin)
Lunes 16 de mayo de 2011 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.


© International Baccalaureate Organization 2011

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ (ፃፊ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ለእለት ተእለቱ ንግግር የምንጠቀምበት አባባል ወይም አገላለጽ ብዙም ትርጉም ላይኖረው ይችላል:: ሆኖም ይህ ንግግር በተዋናዩ በመድረክ ገዝፎና ልዩ ሆኖ ይቀርባል:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን አስረዳ::

2. በድራማ ተመልካቹ አንዳች ውጤት ከድራማው መዋቅር (ፕሎት) ሲጠብቅ ውጥረቱ እያየለ ይሄዳል:: የውጥረቱን ማየልና የሚያስከትለውንም ውጤት ያጠናሃቸውን በሁለት ደራስያን የቀረቡ ሁለት ድራማዎች በመመርኮዝ ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

3. የልቦለድ የፈጠራ አለም ተአማኒ ይሆን ዘንድ ደራሲው የተዋጣ መዋቅር (ፕሎት) ሊያቀርብ ይገባል:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ይህ እንደምን እንደታየ አስረዳ::

4. ድክመቶችና ጉድለቶች ገፀባህርያት ማራኪና ተአማኒ እንዲሆኑ ያደርጋል:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ይህ እንደምን እንደታየ አስረዳ::

**ስነግጥም**

5. ግጥሞች ሙዚቃዊ ለዛ ባለው ቋንቋቸው ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ::

6. ግጥም ለስሜትና ለአእምሮ በመቅረቡና ልዩ በመሆኑ ሌሎች ለግንዛቤ ሲባል በቁንጽልና ግልጽ ባልሆነ መንገድ የሚያቀርቡትን ሀሳብ በተሙዋላና በትክክለኛ ሁኔታ ያቀርባል:: ሀሳቡን ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ አስረዳ::

**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

7. ማንኛውም የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) በግልጽ የተቀመጠ አንድ ሃሳብ ሊኖረው ይገባል:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር የዚህን ሀሳብ ጠቀሜታና የቀረበበትን መንገድ አስረዳ::

8. የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ማጠቃለያ በመጨረሻ የሚነበብና በአንባቢው ላይ ዘላቂ ስሜት ፈጥሮ የሚሄድ ነው:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ይህ እንደምን እንደታየ አስረዳ::



https://xtremepape.rs/

**አጭር ልቦለድ**

**9.** የአጭር ልቦለድ ርእስ ከረጅም ልቦለድ ርእስ በበለጠ ጠቀሜታ አለው:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች የአጭር ልቦለድ ርእስ ያለውን ጠቀሜታና ከስራው ጋር ያለውን ግንኙነት አስረዳ::

**10.** የአጭር ልቦለድ ግጭት በግልጽ የሚታዩ ክርክሮችንና ትግሎችን ብቻ ሳይሆን ማናቸውንም ዋናውን ገፀባህሪ የሚያጋጥሙ በግልጽ የማይታዩትንም ተቃውሞዎች ይመለከታል:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**11.** ስነጽሁፍ የሃሳብ መግለጫ ዘዴ እንደመሆኑ ህይወትን ለመረዳት ያስችላል:: ስነጽሁፍ ህይወትን ለመረዳት እንደምን እንደሚያስችል ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ::

**12.** ስልት ግላዊ በመሆኑ ሁለት የአጻጻፍ ስልቶች ተመሳሳይ ሊሆኑ አይችሉም:: ያጠናሃቸውን ሁለት ደራሲዎች ስልት በጥንቃቄ በመመርመር የሀሳቡን ትክክለኛነት አስረዳ::

**13.** ስነጽሁፍ የሰው ልጆች ጥልቅ ስሜት የሚቀርብበት አንድ መንገድ ነው:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች የሰው ልጆች ጥልቅ ስሜት እንዴት እንደቀረበና ውጤቱም ምን እንደሆነ አስረዳ::

**14.** ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ የሰው ልጆች ውርደትና ክብር ማጣት እንዴት እንደቀረበ አብራራ::



https://xtremepape.rs/